# " በላዕየ-ሰብ ንጉስ "

በታሪክ ከለማው ከአበሻው ምድር፤
ከጀግኖች መቃብር አድዋ መንደር፤
ከዳዋው ከአረሙ ተቀላቅሎ ጉድ፤
ጉርፍ ያመጣው ዝናብ የቁጣው በረድ፤
'ቂጥኝ' አበቀለ ሰብል የሚያነጉድ፣
እርጉም ተወለደ 'በላዕየ-ሰብ ንጉስ' ሐገር የሚንድ፣
ክፉ ንግርት ደርሶ፣ የጥፋት ሰደድ።

'በላዕየ-ሰብ ንጉስ' ዘር ቆጥሮ ከፋፍሎ፣
ዙፋን ሊቀራመት ሕዝብ ሐገሩን ገድሎ።
በደም ባኞ ታጥቦ፣የሰው ቁርበት ለብሶ፣
ስሜት የማይሰጠው የሺዎቹ ለቅሶ።

'በላዕየ-ሰብ ንጉስ'!
እሬሳ አቀላልፎ ጉዝጉዞ እሚተኛ፣
ከ ኤይድስ የከፋ የሕይዎት ቀማኛ፤
ትውልድ ያስቀጸፈ የሕዝብ ደመኛ፣
ከንዋይ ያለፈ ነፍስ-በላ ዳኛ፣
የዘመኑ 'ግራኝ' የባዕዳን ቅጥረኛ።

'በላዕየ-ሰብ ንጉስ'!
መንበረ ሳጥናዔል ውጉዝ ዲያቢሎስ፣
በ'አጋዚያን' ሠራዊት ደም ከንቱ እሚያፈስ፣
የሰው አጥንት ነካሽ 'ጭራቁ' መንፈስ፣
ባንዲራ በሚያጎድፍ ሐገር በሚያፈርስ፣
ታሪክ በሚያጠፉ ሕዝብ እሚያስጨርስ፤
'በላዕየ-ሰብ ንጉስ' 'ዘ-አጼ መለስ'፤
ወገኔ ተነሳ መረብ በመለስ፣
ዘመን ይሻርልን ቅድስ-ዮታንስ።

yegonchaw@yahoo.co.uk
የጐንቻው፡